# ለሕገ ወጥ ዓላማ መጠቀሚያ ከመሆን ተጠበቁ

*ኢ.ብሳ ነመራ 11/16/12*

በያዝነው አመት ሚያዝያ ወር ላይ አካባቢያዊና የማሟያ እንዲሁም የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምርጫ እንደሚካሄድ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሰሞኑን አስታውቃል፡፡ ይህ ምርጫ እንደሚካሄድ የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና በሕዝብ ውሳኔ የስልጣን ውክልና ለማግኘት የሚፎካከሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች አስቀድመውም ያውቁታል፡፡ ምናልባት የማያውቁት ነገር የሚካሄድበት ትክክለኛ ቀን እና እነማን ወክሉን ብለው እንደሚቀርቡ ነው፡፡

ምርጫ ቦርድ ምርጫው እንደሚካሄድ አምናም ከዚያ ቀደምም ያውቁ የነበሩትን ሰባ አምስት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጥቅምት 15/ 2005 ዓ/ም በአዳማ ከተማ ጠርቶ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳውን አቅርቦ አወያይቷል፡፡

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) የተባለው የፓርቲዎች ጥምረት "ከምርጫው የግዜ ሰሌዳ በፊት በምርጫው ዙሪያ መወያየት አለብን" የሚል ጥያቄ አንስቶ በምርጫው ላይ ከሚሳተፉት ሰባ አምስት ፓርቲዎች መሃከል 34 ያህል ፓርቲዎችን ማስተባበሩን ተናግሮ ከምርጫው ለማፈንገጥ መዘጋጀቱን አስታውቋል፡፡

"በምርጫው ፍትሃዊነት ዙሪያ ውይይት ማድረግ አለብን" ብለዋል የተባሉት መድረክ መራሾቹ ፓርቲዎች ሰሞኑን መሰብሰባቸውንም ሰምተናል፡፡

የመድረክ የስራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት አቶ አስራት ጣሴ ሰብሳቢነትን የተፈናጠጡበት ሰላሳ አራቱ ፓርቲዎች አካሄዱት በተባለው ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ ምርጫ ቦርድ በግንቦት ወር በሚካሄደው የአካባቢ ምርጫ አፈፃፀም የግዜ ሰሌዳ ላይ ለመወያየት በአዳማ ከተማ ጥቅምት 15 አዘጋጅቶት በነበረው ስብሰባ ላይ ከጊዜ ሰሌዳው በፊት በምርጫው ፍትሃዊነት ላይ ሊወያዩ እንደሚገባ ለቦርዱ ጥያቄ ማቅረባቸውን ገልፀዋል፡

አያይዘውም ምርጫ ቦርድ በወቅቱ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ ተገቢ ምላሽ ሊሰጣቸው ባለመቻሉ በስብሰባው ላይ ከነበሩት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የጋራ ምክክር አድርገውና

ፔቲሽን ተፈራርመው ጥያቄያቸውን በጋራ ማቅረባቸውን ገልፀዋል፡፡ መድረክ ያሰባሰባቸው ፓርቲዎች "ለጥያቄያችን ተገቢና በቂ ምላሽ ካልተሰጠ ምርጫውን ለማጀብ ፍቃደኛ አይደለንም" ማለታቸውንም ሰምተናል፡፡

እንግዲህ መድረክ እና ከጎኔ አሰልፌያቸዋለሁ ያለን ፓርቲዎች የምርጫው ፍትሃዊነት ላይ እንወያይ ማለታቸው ተነግሮናል፡፡ እዚህ ላይ መድረክና ሌሎቹን ፓርቲዎች አንድ የሚለያቸው ነገር መኖሩን ማስታወስ ግን ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ይህም መድረክ ከሶስት አመት በፊት በአገሪቱ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለወራት መክረውበት የምርጫ ስነምግባር ደንብን ሲያስፀድቁ በራሱ ፍቃድ ይህን ሂደት ረግጦ የወጣ መሆኑ ነው፡፡

በዚህም ምክንያት የምርጫ ስነምግባር ደንቡ ላይ የተስማሙት ፓርቲዎች ከፖለቲካ እንቅስቃሴያቸውና ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሚገጥሙዋቸው ችግሮች ላይ ለመምከር የመሰረቱት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል ሳይሆን ቀርቷል፡፡

መድረክ መራሾቹ ሰላሳ አራት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን፣ የምርጫ ስነምግባር ደንቡን ፈርመው የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መስርተው የመሰረቱት ምክር ቤት አባል ሆነዋል፡፡

ይህ ምክር ቤት በተለይ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያጋጠማቸውና ሊያጋጥመን ይችላል ብልው የሚገምቷቸው ችግሮች ላይ የሚወያዩበት መድረክ ነው፡፡

ሰሞኑን መድረክን እንዳጀቡ የተነገረላቸው 34 ፓርቲዎች ከመጪው የአካባቢ፣ የማሟያና የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምርጫ ጋር በተያያዘ ጥያቄ ካላቸው ራሳቸው የመሰረቱት የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስላለ ጉዳያቸውን እዛ ላይ ማንሳት ይችላሉ፡፡ የጋራ ምክር ቤቱም ያስፈለገው ለዚህ ነው፡፡

በተለይ በዚህ በመጪው ምርጫ ላይ ገዥው ፓርቲ የመወያየት ፍላጎት አላሳየም እንዳይባል፣ የገዥው ፓርቲ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በቅርቡ ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ላይ ካነሳቸውና ውሳኔ ካሳለፈባቸው አጀንዳዎች መሃከል አንዱ ምርጫውን የሚመለከት ነው፡፡

የኢህአዴግ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰሞኑን ያካሄደውን መደበኛ ስብሰባ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ "ምርጫው ሰላማዊ፣ ነፃና ፍተሃዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ አስፈላጊው ሁሉ ይደረጋል" ብሏል፡፡

መግለጫው አያይዞም ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት ጋር በመመካከር ባለፉት አመታት የተጀመረውን ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ የመፍታቱን እንቅስቃሴ ኢህአዴግ አጠናክሮ ይገፋል" ብሏል፡፡

እንግዲህ ይህ ፓርቲዎች የተስማሙበት ሕጋዊ አሰራር እያለ፣ በገዢው ፓርቲም በኩል በችግሮች ላይ ለመወያየት ሙሉ ፍቃደኝነቱ እያለ "ችግሮች አሉ" የሚል ግምት ሲኖር የሚፈታበት ምንም ሕጋዊ ስርዓት የሌለ በማስመሰል አቧራ ለማስነሳት መወራጨት ከየት የመጣ ነው?

እርግጥ ቀደም ሲል እንደተነሳው መድረክን በተመለከተ ያለው ሁኔታ የተለየ ነው፡፡ መድረክ ቀድሞውኑም በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት  በአዋጅ መልክ ፀድቆ የወጣውን የምርጫ ስነምግባር ደንብን ተስማምቶ ለማፅደቅ የተካሄደው ውይይት ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

መድረክ በአህገሪቱ ያሉ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በተሳተፉበት የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ላይ የተደረገ ድርድርና ውይይት ላይ ለአንድ ለሁለት ቀናት ያህል ከተገኘ በኋላ "የኢትዮጵያ ዴሞክረሲያዊ ፓርቲ - ኢዴፓ ያለበት መድረክ ላይ አልሳተፍም፣ ለብቻዬ መደራደር አለብኝ ወዘተ" የሚሉ የማይጨበጡ ሰበቦችን አቅርቦ ነበር ውይይቱን ረግጦ የወጣው፡፡

ምርጫ በዋነኝነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉንም ፓርቲዎች እኩል የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ ሳለ "ይሄኛው ፓርቲ ይውጣ፣ ያኛው ይግባ፣ ለብቻዬ ልደራደር ..." የሚል ምክንያት ማቅረብ በባሕሪው ዴሞክራሲያዊ አይደለም፡፡

እናም ይህ መድረክ ያሳየው ባህሪ ፓርቲው ዴሞክራሲያዊ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በፓርቲዎች መሃከል ሊኖር የሚገባውን መልካም ግንኙነት እንዲሁም ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በውይይት የሚፈቱበትን መንገድ ለመዝጋት በማሰብ የተወሰደ እርምጃ ነው ማለትም ይቻላል፡፡

መድረክ በዚህ አኳኋን የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት አባል ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በመሆኑም በማንኛውም የፖለቲካ ጉዳዮች ምርጫን ጨምሮ የሚገጥሙ ችግሮች ላይ ከሌሎች ጋር የሚወያይበትን፣ የሚደራደርበትን፣ የሚመክርበትን መድረክ በራሱ ፍቃድ ዘግቷል፡፡

ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የምርጫ ስነምግባር ደንቡ ላይ ፈርሞ የፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት አባል የመሆን እድሉ ክፍት ነው፡፡ የጎደለው የፓቲው ፍቃደኝነት ብቻ ነው፡፡

እናም መድረክ አሁን "በመጪው ሚያዚያ የሚካሄደውን አካባቢያዊ፣ የሚሚያና የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምርጫ ላይ ልወያይ" የሚለውን ሰሞነኛ ጥያቄ ያነሳው ሆን ብሎ በራሱ ፍቃድ የዘጋው የውይይት መድረክ የተዘነጋ መስሎት ነው፡፡

በዚህም "የፖለቲካ ምህዳሩ ጠበበብኝ" ብሎ መሰረተ ቢስ ክስ በማቅረብ የተለመደና የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልኛል ብሎ የሙጥኝ ብሎ የያዘውን መንግስትን የማሳጣት ስልቱን የሚያስፈፅምበትን ሁኔታ ከወዲሁ ለማመቻቸት ያሰበ ይመስላል፡፡

ሌላው መድረክ ሰሞኑን ከያዘው አቋም የምንረዳው፣ በምርጫው ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም የሕጋዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ዋነኛ መድረሻ የሆነውን በምርጫ ላይ በመሳተፍ በሕዝብ ውክልና ሕዝብን የማስተዳደር ኃላፊነት ለመረከብ የተዘጋጀን ዕድል እንደዋዛ መተው፣ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያሳጣ፣ በመጨረሻም እንደሚያስረሳ ያውቀዋል፡፡

ስለዚህ ቢያሳምንም ባያሳምንም ከምርጫው የሚሸሽበትን ማመካኛ ሰበብ ማበጀት ይኖርበታል፡፡ ሰሞኑን የያዘው ከምርጫው በፊት ልወያይ የሚል ጥያቄ ዓላማም ይሄው መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

አንድነት/መድረክ መጪው ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት የሌለው መሆኑን፣ አመራሮቹ በቅርቡ ሰሜን አሜሪካ ሄደው ለማይመርጣቸው ሕዝብ ያወሩት ነገር ያመላክታል፡፡

ምርጫ ላይ መሳተፍ የማንኛውም የፖሊተካ ፓርቲ የማይጠየቅ አቋም ሆኖ ሳለ የመድረክ/አንድነት አመራሮች ሰሜን አሜሪካ ሄደው "እስካሁን መሳተፍ አለመሳተፋችን ላይ አልወሰንም" ማለታቸውን ሰምተናል፡፡

በማንኛውም አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ መንግስትን አስወግዶ ስልጣን ላይ የመውጣት ሕልም ያለውና ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነው የምርጫ አካሄድ ለዚህ እንደማያዋጣው የሚያውቀው ዳያስፖራው ታጋይ ደግሞ "ምርጫ ላይ አትሳተፉ፣ ይሄው የትግል ታክቲኩ፣ ይሄው ማስፈፀሚያ ገንዘቡ" ብሎ መልሶ ወደ አገር ቤት እንዳሰማራቸው ብዙዎች ገምተዋል፡፡

እዚህ ላይ "መድረክ ምርጫው ላይ እንዳይሳተፍ የሚያደርገው ድርጅታዊ ሁኔታ ምንድነው?" የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ነገሩ ሰፊ ነው፡፡ በአንድ የጋዜጣ ጽሁፍ ማንሳት የሚቻለውን ያህል እንመልከት፡፡

በቅድሚያ መድረክ የተሰኘው የፓርቲዎች ስብስብ ቀድሞውንም ከአመሰረሰረቱ ምርጫ ላይ መሳተፍ ተቀዳሚ ዓላማው አይደለም የሚል ጥርጣሬ ይፈጥራል፡፡ በስሩ የተሰባሰቡት ፓርቲዎች አቋምና ፖሊሲ የተለያየና እርስ በርስ የሚጣረስ መሆኑ ይህን ያመለክታል፡፡

ሌላው መድረክን ከምርጫ እንዲሸሽ የሚያደርገው በስሩ የተጣመሩት ፓርቲዎች አቋሞችና ፖሊሲዎች የተለያዩና ተቃራኒ በመሆናቸው የተነሳ  ምርጫ ላይ ቢቀርብ አላሸንፍም የሚል ግምት ያለው ይመስላል፡፡

የዚህ  የሽንፈት ስጋት መሰረታዊ ምክንያት መድረክ የተሰኘው ስብስብ ከያዛቸው ፓርቲዎች ፖሊሲና አቋም የሚመነጭ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

መድረክ በርካታ ፓርቲዎች መሰባሰባቸው ብቻውን መንግስትን መገዳደር የሚችል ኃይል እንደሆነ ያምናል፡፡ የፓርቲዎች ግንባር መፍጠር ኃይል መሆኑ እርግጥ ቢሆንም፣ የአቋም መመሳሰል በሌለበት ሁኔታ ግን አቅም ከመሆን ይልቅ የደካማነት ምንጭ ነው የሚሆነው፡፡

ቀደም ሲል እንዳነሳነው መድርክ ያሰባሰባቸው በተለይ እንጋፉ ነን የሚሉት ፓርቲዎች ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን ከስልጣን ከማስወገድ ፍላጎት ውጪ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ ማለት ስህተትነቱ ያይላል፡፡ ከዚህ ውጭ ባሉ ጉዳዮች ያላቸው አቋም ካለመመሳሰልም አልፎ ተቃራኒም ጭምር ነው፡፡

ለአብነት ያህል መድረክ ውስጥ አይነ ግብ ነን የሚሉትን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት)፣ በበየነ ጴጥሮስ የመመራው ሕብረት፣ የዶ/ር መራራ ጉዲናን የኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ - ኦህኮ እንመልከት፡፡

አንድነት የሊበራል ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መርሕ ተከታይ እንደሆነ ነው የሚናገረው፡፡ ፖሊሲዎቹም በዚህ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት ፓርቲው ለግለሰብ መብት እንጂ ለቡድን መብት ዕውቅና የማይሰጥ አይሰጥም፡፡ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ገንኖ ለወጣውና የፖለቲካውን አቅጣጫ ለወሰነው የብሄር ብሄረሰብ ጥያቄ እውቅና ይነፍጋል፡፡

በመሆኑም በሕገመንግስቱ ላይ የተደነገገውን በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌዴራላዊ አወቃቀር አይደግፍም፡፡ አንድነት እንደ አማራጭ የሚያቀርበው መልከአምድራዊ ፌደራላዊ አወቃቀርን ነው፡፡

መልከአምድር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ግዛቶች አወቃቀር ማለት፣ በንጉሠነገሥቱ የጠቅላይ ግዛት በኋላም በደርግ ክፍለ ሃገር መሰረት ወንዝ፣ ተራራ፣ ሸለቆ ...ላይ የተመሰረተ አወቃቀር አይነት ማለት ነው፡፡

በዚህ ለሕዝብ ማንነት ዕውቅና የነፈገ አወቃቀር አንድ ማንነት ያለው ብሄር፣ ብሄረሰብ ወይም ህዝብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ቦታ ሊበጣጠስ ይችላል፡፡

ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ወይም ህዝቦች ደግሞ በአንድ አስተዳደር መዋቅር ውስጥ ለጨፈለቁ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ራስን በራስ ማስተዳደር የሚለው ጉዳይ የማይታሰብ ነው፡፡

ይህ መድረክ የሚያቀርበው አማራጭ በአሁኑ ግዜ እጅግ በጣም ጥቂት ካለፉ ስርዓት አመለካከት ውርዴነት ባልተለቀቁ ዜጎች ካልሆነ በስተቀር እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ተቀባይነት የሌለው መሆኑ እርግጠኛ ነው፡፡

በሌላ በኩል በመድረክ ስር ከአንድነት ጋር የተጣመሩት እንደ ህብረት፣ ኦህኮ ያሉ ፓርቲዎች በዚህ በፌዴራላዊ አወቃቀር ላይ የያዙት አቋም የተለየ ነው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የፌዴራሊዝም አወቃቀርን በተመለከተ ያየዙት አቋም “አወቃቀሩ በብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት” የሚል ከህገመንግስቱ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡

ወደ መድረክ ፓርቲዎች የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመለስ በተለይ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ድረሻ ያለው የመሬት ይዞታ ጥያቄ ላይ ሊበራል ዴሞክራት ነኝ የሚለው አንድነት፣ “መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ሀብት መሆን አለበት” ይላል፡፡

በሌላ በኩል ሶሻል ዴሞክራት ነን የሚሉት ህብረት፣ ኦህኮና ሌሎችም የተወሰኑ የመድረክ ፓረቲዎች “መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝብ ሀብት መሆን አለበት” የሚል አቋም አላቸው፡፡

እነዚህ በመሰረታዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተቃራኒ አቋም ያላቸው ፓርቲዎች ግን መድረክን ከመሰረቱ በኋላ በተናጥል የሉም፡፡ ቢያንስ በተናጥል የለንም ብለው በይፋ ነግረውናል፡፡

ምርጫው ላይ ሊበራል ዴሞክራቱ አንድነትና ሶሻል ዴሞክራቱ ህብረት ለየብቻ አይቀርቡም፡፡ ተቃራኒያቸውን አዝለው መድረክ በሚል ስያሜ በአንድ የምርጫ ምልክት ነው የሚቀርቡት፡፡

እናም መድረክ ሲሆኑ በተናጠል ባላቸው አቋም ሊደግፏቸው ይችሉ የነበሩ ዜጎች ተጣምረው ሲመጡ ያዘሉትን ተቃራኒያቸውን ሸሽት ድምፃቸውን መንፈጋቸው አይቀሬ ነው፡፡

በዚህ አኳኋን መጣመራቸው ከመደጋገፍ ይልቅ ተያይዞ ለመውደቅ አደጋ አጋልጧቸዋል፡፡ እንግዲህ የመድረክ ፓርቲዎች ይህን ለውድቀት ያጋለጠ ጥምረታቸውን አያውቁትም የሚል ግምት የለኝም፡፡

የሕዝብ ድምፅ እጦቱን ግን በፀጋ መቀበል  አይፈልግም፡፡ በመሆኑም እነሱም እንዳሉት ምንም ድምፅ በማያገኙበት ሁኔታ መሸነፋቸው አይቀሬ የሆነበተ ምርጫ ውስጥ መግባት "የምርጫ አጃቢ" ከመሆን ውጭ የትም እንደማያደርስ ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ ሕዝብን የሚያደናግር ሰበብ ፈልጎ ከምርጫው ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡

መድረክ ያሰባሰባቸው እርስ በርስ የሚጣረስ አቋምና ፖሊሲ ያላቸው ፓርቲዎች ከላይ እንደተገለፀው የህዝብ ድምፅ ማግኘት እንደማይችሉ  ካወቁ "በጋብቻቸው መቀጠል ለምን ፈለጉ? ለምን አይፋቱም?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

የመድረክ ፓረቲዎች ምፋታት ያልመረጡት ቀድሞውንም የተጋቡት በዋናነት እንደ አንድ ግንባር አንድ አቋም፣ ተመሳሳይ ፖሊሲ ይዘው በምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ አይደለም፡፡የዚህ አይነት አቋም ቢኖራቸው ኖሮ ለአቋምና ለፖሊሲ ተመሳሳይነት ቅድሚያ ይሰጡ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለጋብቻ ያስተጫጪቻው በምርጫ አሸንፎ የመንግስት ሰልጣን መረከብን ዋና ዓላማ ያላደረጉ በጭፍን ጥላቻ የሚመሩ በውጭ አገራት የሸፈቱ ታጋዮች መሆናቸው የመድረክ ፓርቲዎች ፍቺውን በራሳቸው ፍቃድ የመፍፀም ወኔም፣ የውሳኔ አቅምም አሳጥቷቸዋል፡፡

በዚያም በዚህም የመድረክ ፓርቲዎች ጥምረት መነሻ፣      በምርጫ ከሚገኝ የህዝብ ውክልና ውጭ በማንኛውም አመቺ በሆነ መንገድ ስልጣን የመያዝ ፍላጎትና  የዚህ አይነት ፍላጎት ባላቸው የውጭ አገር ሽፍቶች ምክር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እነዚህ በውጭ ያሉ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የሚመሩት በህዝብ ፍላጎትና ዘላቂ ጥቅም ሳይሆን፣ ገዢው ፓርቲና ሕገመንግስታዊ ስርአቱ ላይ ባላቸው ጭፍን ጥላቻ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

በውጭ አገራት የሸፈቱ በጭፍን የጥላቻ ፈረስ የሚጋልቡ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች አመቺ ሆኖ ባገኙት አጋጣሚ ስልጣን ላይ ለመውጣት ካለ ፍላጎት ውጭ ለሕዝብ መብት፣ ነፃነት፣ እድገት፣ የተሻለ ሕይወት መኖር …ቅንጣት ታክል አይጨነቁም፡፡

በመሆኑም ገዢው ፓርቲና ሕገመንግስታዊ ስርአቱ ላይ ተመሳሳይ ጭፍን ጥላቻ አላቸው ብለው ከገመቱዋቸው በአገር ውስጥ ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ፖሊሲያቸውና አቋማቸው ምንም ይሁን ምን ይፈልጉዋቸዋል፡፡

ፓረቲዎቹ በዚሁ በሚያመሳስላቸው መሰረተ ቢስ ጥላቻ ላይ ተመስርተው በአንድ ግንባር እንዲሰለፉም ይፈልጋሉ፡፡ በጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ በርካቶችን ያሰባሰበ ቡድን ወይም ግንባር ሕገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ መንግስትን በማስወገድ ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚያስችል ኃይል ሆኖ ነው የሚታያቸው፡፡

በዚህ አኳኋን በወጭ አገር ታጋዮች ላይ የተለጠፉ ፓርቲዎች ወይም ስብስባቸው በምርጫ የሕዝብ ድምፅ ማግኘት ወይም አለማግኘት ቀዳሚ አላማቸው አይሆንም፡፡ ከዚህ ይልቅ በሕግ ከለላ ስር ሆነው አመቺ ነው ያሉት አጋጣሚ ሲኖር ይህን ተጠቅመው ወደ ሕገወጥነት ለመሄድ ሁሌም በንቃት መጠባበቅ ላይ ያተኩራሉ፡፡ ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ መስመር ውስጥ መግባት የሚያስፈራቸው ለዚህ ነው፡፡

ለምሳሌ መድረክ የተሰኘው የፓርቲዎች ስብስብ አገሪቱ ውስጥ ካሉት ሁሉም ተቃዋሚ ፓረቲዎች ተነጥሎ የምርጫ ስነምግባር ደንቡ ላይ መወያየት፣ ተስማምቶ መፈረም፣ በመጨረሻም በዚሁ ደንብ መሰረት የተቋቋመው የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል መሆን ያልፈለገው ለዚህ ነው፡፡

የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ አንዳችም ችግር እንደሌለበት ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ በዚህ ደንብ ላይ ተስማምቶ ይህግ ማዕቀፍ ውስጥ መግባት ግን የሕግ ወጥ እንቅስቃሴን መንገድ ይዘጋዋል፣ ቢያንስ ያጠበዋል፡፡

እናም የመድረክ ፓርቲዎች መፋታት ያላስፈለጋቸው ወይም የማይችሉት፣ አንድም በምርጫ ተወዳድሮ አሸንፎ ስልጣን መረከብ ቀዳሚ ዓላማቸው ባለመሆኑ፣ ሌላም ያጋቧቸው ሰላማዊ መንገድ የሚጎመዝዛቸው ውጫዊ ኃይሎች በመሆናቸው ነው፡፡ የሚንቀሳቀሱበት ገንዘብ፣ የእንቅስቃሴ አቅጣጫቸውን በአብላጫው የመያስገቡት አጋቢዎቻቸው ከሚገኙባቸው አገራት ነው፡፡

በቅርቡ የመድረክ አንድነት አመራሮች ሰሜን አሜሪካ ሄደው የነበረውም ለዚህ ነው፡፡ የምርጫ ቅስቀሳ ሊያደርጉ አለመሄዳቸው ግልፅ ነው፡፡ አቋማቸውን ከቀየሩ ወይም የታዘዘላቸውን ጋብቻ ካፈረሱ ውጉዝ ከመአርዮስ ተብለው ማረፊያ ያጣሉ፡፡

ዋና መነሻችን ወደሆነው መድርክ ሰሞኑን ወዳነሳው አጀንዳ ስንመለስ፣ “ከምርጫው በፊት…” የሚል ተጎታች ይዞ የተነሳው ቀደም ሲል እንደተገለፀው እንደማያሸንፍ በእርግጠኝነት የተገነዘበውን የአካባቢ፣ የሚሚያና የአዲስ አበባ ምክር ቤት ምርጫ፣ ከሕጋዊና ሰላማዊ ውጭ ለሆነ ስልጣን ማግኘት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር እንደ አንድ ሁነት/event/ ከመጠቀም ፍላጎት የመነጨ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከምርጫው በፊት መወያየት አለብን በሚል በመድረክ መሪነት እንደተሰበሰቡ የተነገረን ፓርቲዎች ባደረጉት ስብስባ ላይ ለምርጫ ቦርድ የቀረበው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ካልተሰጠው፣ ሰላማዊ ሰልፍን ጨምሮ ሕዝባዊ ንቅናቄ እስከመፍጠር የዘለቀ እርምጃ እንወስዳለን በሚል ያቀረቡት ዛቻ አዘል ሃሳብም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት መድረክ አደናግሮ ዓላማውን ለማሳካት በአጃቢነት ከጎኑ እንዳሰለፋቸው የነገረን ሰላሳ አራት  ፓርቲዎች ሰላማዊ ሰልፍም፣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴም ሳያስፈልጋቸው “አለ” የሚሉት ችግር ላይ መወያየት የሚያስችል መድረክ አላቸው፡፡

እርግጥ መድረክ ይህን ዕድል የመጠቀም ፍላጎት እንደሌለው በተግባር አሳየቷል፡፡ ከውይይትና ድርድር የተሻለ ወደ ስልጣን ለመውጣት የሚመች ስልት ማበጀት የሚያስችል አቋራጭ አለ ብሎ ስላመነ ወይም እንዲያምን ስልተደረገ ነው እድሉን ንቆ የተወው፡፡ አሁንም ፍቃደኛ ከሆነ  የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ላይ ፈርሞ “አለ” የሚለው ችግር ላይ ከሁሉም ፓርቲዎች ጋር ገዢውን ፓርቲን ጨምሮ መወያየት ይችላል፡፡

ያም ሆነ ይህ መድረክ ምርጫን አስታኮ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፀደቀው የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ፣ እንዲሁም በይፋ የፍርድ ሂደት በፍርድ ቤት ውሳኔ ቅጣት የተወሰነባቸው ግለሰቦች ጉዳይ አንስቶ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድና ሕዝባዊ ንቅናቄ ለመፍጠር ማሰቡን ነግሮናል፡፡ በዚህም የህግ የበላይነትን የሚፃረር ሰላማዊ ያልሆነ አካሄድን የመከተል አዝማሚያ እያሳየ መሆኑ መስተዋል አለበት፡፡

ይህ የመድረክ አካሄድ የተለመደና በስሩ ከተጣመሩት ፓረቲዎች ባህሪ የመነጨ ነው፡፡ ሰሞኑን አጃቢዎቹ ይሆኑ ዘንድ የጀነጀናቸው ፓርቲዎች ለዚህ የህግወጥነት አዝማሚያ ለሚታይበት የመድረክ አካሄድ ማስፈፀሚያ መሳሪያ ላለመሆን መጠንቀቅ አለባቸው፡፡

ከገዢው ፓርቲም ሆነ ከሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር መወያየት አለብን የሚል እምነት ካላቸው ራሳቸው የመሰረቱት የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አለላቸው፡፡ችግራቸውን በዚህ መድረክ ላይ አንስተው መወያየት ይችላሉ፡፡ እናም ሁኔታውን በሀላፊነት ስሜት አጢነው ራሳቸውን ከመድረክ መነጠል አለባቸው፡፡ ለሕገ ወጥ ዓላማ መጠቀሚያ ላለመሆን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡